Federal Urban Job Creation & Food Security Agency

## አጋሮች/ Partners

ARRA
Agency for Refugees and Returnees Affairs

በስ.ጉ.ኤ የተተገበረ
Implemented by ARRA

በአውሮፓ ህብረት ገንዘብ ተደገፈ
Financed by the European Union


# ምስጋና

ይህ ጋይድላይን የተዘጋጀው በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው:: የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በጋይድላይኑ ዝግጅት ላይ ለተሳተፉ ባለሙያዎች፣ አስተዋጾ አድራጊዎች፣ አራሚዎችና አጋሮች ጥልቅ ምስጋናውን ይገልፃል::


# ማሳሰቢያ

ይህ ጋይድላይን የተዘጋጀው በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው:: በመሆኑም በሰነዱ ላይ የተካተቱት ሀሳቦች በሙሉ የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን የሚወክሉ/ የሚመለከቱ ሲሆን በየትኛዉም መልኩ የአውሮፓ ህብረትን እና የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲን ሃሳብ ወይም አቋም የሚያንፀባርቅ አይደለም::

# ማውጫ


ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ---------- 1

1. መግቢያ ---------- 1

1.2. ትርጓሜ ---------- 1

1.3. ዓላማ ---------- 3

1.4. አስፈላጊነት ---------- 4

1.5 መርሆዎች ---------- 4

ክፍል ሁለት፡- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአደረጃጀት ሁኔታ ---------- 5

2.1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች ልየታ ---------- 5

2.2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የምልመላ ሂደት የሚሳተፉ አካላት ---------- 6

2.2.1 ከተማ/ወረዳው በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የምልመላ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት 7

2.3. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ አይነቶች ---------- 8

2.4. በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ዜጎች የአደረጃጀት ሁኔታ ---------- 9

2.4.1 የህጋዊ ሰውነት አሰጣጥ ---------- 9

2.4.2 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚደራጁ ማህበራት የአባላት ብዛት ሁኔታ 9

ክፍል ሶስት፡- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአሰራርና ሽግግር ---------- 10

3.1 የስራ ትስስር ሂደት ---------- 10

3.2 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ማህበራት የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች 10

3.3 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ማህበራት ቆይታ ጊዜ ---------- 11

3.3.1 በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ማህበራት ቆይታ ጊዜ ---------- 12

3.4 ከጥሪት ማፍሪያ የስራ ዘርፎች ወደ መደበኛ የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ---------------- 13

3.5 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚደራጁ ማህበራት መብትና ግዴታ -------------- 14

3.5.1 የማህበራቱ መብት ---------------------------------------------------------- 14

3.5.2 የማህበራቱ ግዴታዎች ------------------------------------------------------ 14

ክፍል አራት፡- የፈፃሚና የባለ ድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት -------------- 16

ክፍል አምስት፡- ክትትልና ድጋፍ፣ ግብረ መልስ ---------------------------------- 22

ክፍል ስድስት፡- የተፈጻሚነት ወሰን ------------------------------------------------ 22

ክፍል ሰባት፡- ጋይድ ላይኑን ስለማሻሻል ------------------------------------------ 23

ክፍል ስምንት፡- ጋይድ ላይኑ ስለሚጸናበት ሁኔታ ------------------------------ 23

አባሪዎች ------------------------------------------------------------------------------------ 24

አባሪ አንድ፡- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ማህበራት ውል ማስገቢያ ሰነድ 24

አባሪ ሁለት፡- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሚሰማሩ ማህበራት የአደረጃጀት የምስክር ወረቀት 28

# ክፍል አንድ፦ አጠቃላይ

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ከተሞች ጎልቶ የሚታየው ስር የሰደደ ድህነት ከመሰረቱ ለማስወገድና የሚስተዋለዉን የስራ አጥነት ችግር በመቅረፍ የሀገራችን ከተሞች መካከለኛ ገቢ ካላቸው ከተሞች ተርታ ለማሰለፍ ፈጣን፤ መሰረተ ሰፊ፤ ሁሉን አቀፍ እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ መንግስት የተለያዩ ስትራቴጅዎችና ፖሊሲዎችን ቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሰረት የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአደረጃጀትና አሰራር ጋይድ ላይን በ2010 ዓ.ም በማውጣት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ዜጎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ በማሰማራት ሃብት አፍርተው ወደ መደበኛው የስራ እድል ፈጠራ እንዲሸጋገር ከማድረግ አንጻር አፈጻጸሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ ምክንያትና የፌደራሉ መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን መዋቅር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011ዓ.ም እንደገና መቋቋሙን መሰረት በማድረግ በየደረጃው ያሉ የመንግስት ተቋማትን አደረጃጀት የቅርጽና የመጠን እንዲሁም ስልጣንና ተግባር ለውጥ መደረጉን ተከትሎ ጋይድ ላይኑን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም ለጥሪት ማፍሪያነት የተመረጡ ሃብቶች ውስን በመሆናቸውና በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የመነሻ ካፒታል ለሌላቸው ስራ ፈላጊዎች በተቀናጀ መልኩ ወደ ስራ በማስገባት ወደ መደበኛ የስራ እድል ፈጠራ ለማሸጋገር እንዲቻል እና ውስን የሆነውን የሀገሪቱን ሃብቶችና ፀጋዎች በአግባቡ በመጠቀም ለስራ ፈላጊ ወጣቶች የሀብት መፍጠሪያ እንዲሆኑ ለማስቻል ይህ ጋይድላይን ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. ትርጓሜ

1. “የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ” ማለት የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሕጋዊነትን ለማስፈን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የመንግስታዊ ድጋፎች በተቀናጀ መልኩ ከአንድ ስፍራ በአንድ አስተባባሪ አካል ሥር ካሉ አካላት የሚያገኙበት አደረጃጀት ነው፡፡
2. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47/1/ የተመለከቱትን ክልሎች እና አዲስ የተቋቋመውን የሲዳማ ክልልን ጨምሮ ማለት ሲሆን ለዚህ ማንዋል አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፡፡
3. “ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት እና 2 ሺህ ወይም ከዚህ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

4. “የከተማ አስተዳደር” ማለት ቻርተር ያላቸውን ከተሞች ሳይጨምር በሌሎች ከተሞች ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት ያለ የከተማ አስተዳደርና አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው::
5. ”የክልል ኤጀንሲ ወይም ቢሮ” ማለት በየክልሉ የተዋቀሩ የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ሥራን የሚደግፍና የሚያስተባብር አካል ነው::
6. “ስራ ፈላጊዎች” ማለት ዕድሜያቸው 18 እስከ 60 ዓመት የሆናቸው፣ የመሥራት ፍላጐትና ችሎታ እያላቸው የራሳቸውን ሥራ በመፍጠርም ሆነ በመቀጠር ቋሚ የሥራ መስክ የሌላቸውን፤ ያልተማሩትንና በተለያየ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ የሀገሪቱ ዜጐች ሁሉ ሥራ ፈላጊዎች ተብለው ይመዘገባሉ::
7. “የጥሪት ማፍሪያ“ ማለት በተወሰኑ አካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቶችንና ፀጋዎችን በመጠቀም ለመነሻ ካፒታልነት የሚረዳ ገቢ ማስገኛ የስራ መስክ ማለት ነው::
8. “የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ምሩቃን ስራ ፈላጊዎች” ማለት ከመንግስትና ከግል ዩኒቨርሲቲዎች በዲግሪና ከዚያ በላይ፣ ከመንግስትና ከግል ኮሌጆች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከደረጃ I-V የተመረቁና በዘርፉ የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ፍላጎት ያላቸው ማለት ነው::
9. “የሥራ ዕድል ፈጠራ” ማለት የመስራት አቅም እና ፍላጎት እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ስራ ያልገቡ ዜጎችን በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የስራ ዘርፎች ማሠማራት ነው::
10. “ቋሚ የሥራ ዕድል” ማለት የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ ፈጥረው የሚሰሩ ወይም በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በፔይሮል ክፍያ በማግኘት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው::
11. “ጊዜያዊ የሥራ ዕድል” ማለት የተፈጠረ የስራ ዕድል ሲሆን ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ክፍያ ለማግኘት ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው::
12. “ሽግግር” ማለት አንቀሳቃሾች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ ወይም በፈጠሩት የካፒታል ጣሪያ መጠን ወደ መደበኛ ዘርፎች ማሸጋገር ማለት ነው::
13. የውዴታ ግዴታ ቁጠባ ማለት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ አንቀሳቃሾች በቆይታ ጊዜያቸው ለቀጣይ ስራ መቋቋሚያ /መነሻ ካፒታል እንዲሆናቸው በየጊዜው ከሚያገኙት ገቢ 30 በመቶ የሚቆጥቡት ገንዘብ መጠን ማለት ነው::
14. “ሥልጠና“ ማለት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሚሰማሩ አንቀሳቃሾች በንግድ ሥራ አመራርና በቴክኒክና ሙያ የሠልጣኞችን አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድግና በአዎንታዊ መልኩ የባህሪና የአሰራር ለውጥ የሚያመጣ የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የመማማር ሂደት ነው::
15. “የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና” ማለት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሚሰማሩ አንቀሳቃሾች ምርት ወይም አገልግሎት በብቃት ለማቅረብ፣ ጥራትና ምርታማነትን በቀጣይነት ለማሻሻል፣ የፈጠራ ሥራዎችን ለማበረታታት፣ አመለካከትን፣ ዕውቀትና ክህሎትን

በማሳደግ በተሰማሩበት ወይም በሚሰማሩበት መስክ ላይ እሴትን በመጨመር ልማትን ለማፋጠን እንዲያስችል የሚሰጥ ሙያዊ ሥልጠና ነው፣

16. “የንግድ ሥራ አመራር ሥልጠና” ማለት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሚሰማሩ አንቀሳቃሾች አዋጪ የንግድ መስክን በመምረጥ፣ በማቋቋምና በመምራት ሂደት ውስጥ በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበርና በመቆጣጠር ውጤታማ እንዲሆኑ የሚሰጥ ሥልጠናው፣

17. “ማምረቻ መሳሪያ” ማለት የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ምርትን ለማምረት እና አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ የተለያዩ በሰው ሐይል ፣ በእንስሳት ጉልበት የሚሳቡ እና በአማራጭ የሃይል ምንጮች የሚሰሩ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ማለት ነው::

18. “ፈጻሚ አካላት” ማለት ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ላሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ለመስጠት የተዋቀሩ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች እና አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ያጠቃልላል::

19. “የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ” ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በበላይነት የሚመራ የፌደራል ኤጀንሲ ነው::

20. ”አነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት” ማለት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ፣ ብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ማለት ነው::

21. “የገበያ ትስስር” ማለት ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድል ለመፍጠር ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፤ በሀገር ውስጥ በግብዓት፤ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት (በግዢና ሽያጭ) በጎንዮሽና በተወረድ ግንኙነት የሚፈጠር የገበያና ግብይት ሥርዓት ነው::

22. “መነሻ ካፒታል“ ማለት ማንኛውም ስራ ፈላጊ ወደ ስራ ለመግባት የሚያስፈለግ መነሻ ሀብት ማለት ነው::

## 1.3. ዓላማ

በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚሰማሩ ዜጎች ከኪራይ ሰብሳቢነት በፀዳ መልኩ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ መነሻ ካፒታል አፍርተውና ልማታዊ አስተሳሰብ ፈጥረው ወደ መደበኛ የስራ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የዘርፉ ዕድገት ቀጣይነት እንዲኖረው የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማድረግ ነው::

# 1.4. አስፈላጊነት

1. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች አደረጃጀት፣ አሰራርና ሽግግር ህግና ስርዓት ተዘርግቶለት ወጥና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለመተግበር በማስፈለጉ፣

2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ምሩቃን፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች መነሻ ካፒታል የሌላቸውና ሀብት አፍርተው ወደ ዕድገት ተኮር ዘርፎች በማሸጋገር የሀብት ክፍፍሉን ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በማስፈለጉ፣

3. ጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች በባህሪያቸው ዘላቂነት የሌላቸውና የመሸጋገሪያ የስራ መስኮች በመሆናቸው በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ አንቀሳቃሾች ወደ እድገት ተኮር ዘርፎች በማሰማራት ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥና ለመደገፍ፣

4. እሴት በማይጨመርባቸዉ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ ስራ ፈላጊዎች እንዴት ወደ ድጋፍ መዕቀፉ የሚገቡበትና የቆይታ ጊዜያቸዉን ሲያጠናቅቁ ወደ ቀጣይ የሚሸጋገሩበት ስርዓት ለመዘርጋት በማስፈለጉ ነዉ፣

5. እሴት በማይጨመርባቸዉ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ ህጋዊ ፍቃድ ወስደዉ ስራ ላይ ያሉ እንዴት ወደዚህ ስርዓት የሚገቡበትን አሰራር ለማስተካከል፣

# 1.5 መርሆዎች

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ዜጎች ህግና ስርዓት ተዘርግቶለት ወጥና አሳታፊ በሆነ መልኩ መነሻ ካፒታል እንዲያፈሩ ማድረግ፣

2. ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነትና ግልፅኝነት የሰፈነበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ ማህበራት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ወይም የሃብት መጠን መነሻ ካፒታል አፍርተው ወደ መደበኛ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ ማስቻል፣

4. የወጣቶች፣ የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

5. የአካባቢና የተፈጥሮ ሃብቶችን ደህንነት የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣

6. በአከባቢው የሚገኙ ለጥሪት ማፍሪያነት የሚዉሉ ሃብቶችን አሟጦ መለየትና በአግባቡ መጠቀም፣

# ክፍል ሁለት

# 2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአደረጃጀት ሁኔታ

## 2.1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች ልዩታ

በመደበኛዉ የስራ ዕድል ፈጠራ ለመሰማራት ፍላጎት እያላቸዉ የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ወጣቶች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ተሰማርተዉ ጥሪት እንዲያፈሩ ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ካሉን ዉስን የተፈጥሮ ሃብትና የአካባቢ ፀጋ አንፃር ፍላጎት ላለዉ ሁሉ ማዳረስ ስለማይቻል በዘርፉ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወጣቶችን መለየት አስፈላጊነቱ እሙን ነዉ፡፡

- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች መመልመያ መስፈርቶች

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በስራ ፈላጊነት ከተመዘገቡት ስራ ፈላጊዎች ብቻ ይሆናል፣
2. የሚመለመሉ ስራ ፈላጊዎች በስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ ምዝገባ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም ማኑዋል ቁጥር 001/ 2009 በተቀመጠው አሰራር መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፣
3. በስራ ፈላጊዎች የትምህርት ደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት (የዩኒቨርሲቲ፣ የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን እና ሌሎች ስራ ፈላጊዎች) ሆኖ ስራውን ለመስራት ዝግጁነት ያለው/ያላት፤
4. ወደ መደበኛ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸውን የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ብቻ የሚመቻች ይሆናል፣
5. ከሌሎች ስራ ፈላጊዎች ጋር በቡድን ተደራጅቶ ለመስራትና ለመለወጥ ፈቃደኛ የሆነ/ች፤
6. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ተሰማርቶ ከሚያገኘው ገቢ የተቀመጠውን የግዴታ ቁጠባ ለመቆጠብ ፈቃደኛ የሆነ/ች፣
7. በተቀመጠው የቆይታ ጊዜ ወይም ጥሪት ማፍሪያ ስራ ሲጀምር ባዘጋጀው ንግድ ስራ ዕቅድ 20 ከመቶ መነሻ ካፒታል መሰረት ወደ መደበኛዉ ዘርፍ ለመሸጋገር ፈቃደኛ የሆነ/ች፣
8. ሙሉ ጊዜውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስራት ቁርጠኛ አቋም ያለው/ላት፣
9. ከዚህ ቀደም በጥሪት ማፍሪያም ሆነ በሌሎች የስራ ዘርፎች ተደራጅቶ የማያውቅ/የማታውቅ፣
10. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም በአካባቢ ልማት ላይ የታቀፉ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ መሳተፍ የለባቸውም፣

# 2.2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የምልመላ ሂደት የሚሳተፉ አካላት

በጥሪት ማፍሪያ ዘርፍ ለመሰማራት የሚመለመሉ ስራ ፈላጊዎች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በስራ ፈላጊነት ከተመዘገቡት መካከል ሆኖ ካለው የሃብት ውስንነት የተነሳ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ለይቶ ማስተናገድ እንዲቻል እንዲሁም የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመለየት የሚሳተፉ የኮሚቴ አደረጃጀትና ስብጥር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- በከተማ/ወረዳ ደረጃ የሚኖር አደረጃጀት፣

1. የከተማ/ወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ ---------------------------------------------- ሰብሳቢ
2. የከተማ/ወረዳው የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ኃላፊ----ም/ሰብሳቢና ፀሀፊ
3. የከተማ/ወረዳው ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------- አባል
4. የከተማ/ወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------------ አባል
5. የከተማ/ወረዳው የሴቶች፣ የህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት ኃላፊ ---------------------- አባል
6. የከተማ/የወረዳው ማዕድንና ኢነርጂ ጽ/ቤት ኃላፊ------------------------------------ አባል
7. የከተማ/ወረዳው አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ -------------------------------------------አባል
8. የከተማ/ወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ----------------------------------------------- አባል
9. የከተማ/ወረዳው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ተወካይ --------------------------- “
10. የከተማ/ወረዳው የብድርና ቁጠባ ስራ አስኪያጅ --------------------------------------- “
11. የከተማ/ወረዳው የወረዳው ወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ----------------------------------- “
12. የከተማ/የወረዳው ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ ---------------------------------------------- “
13. የከተማ/የወረዳው ነዋሪዎች ፎረም ሰብሳቢ ------------------------------------------ “
14. በከተማ/ወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ መካተት ያለባቸው ሌሎች አደረጃጀቶች አባል ሆነው ይደራጃል፡፡

## 2.2.1 ከተማ/ወረዳው በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የምልመላ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸውን የቅድመ ብደር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች የሚውል ተጨማሪ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮችን መለየት፣
2. ከዚህ ቀደም ለባለሀብቶች የተሰጡ የአካባቢ የተፈጥሮ ሃብቶች ለስራ ፈላጊ ወጣቶች የጥሪት ማፍሪያነት እንዲዉል ከሚመለከታቸዉ አካላት በመነጋገር በፍቃድም ሆነ ያለፍቃድ ስራ ላይ ያሉ በመለየት እንዲመልሱ ማድረግ፣

3. በአካባቢው የሚገኙ በጥሪት ማፍሪያ የተለዩ የስራ መስኮችን አቅም መነሻ በማድረግ ስራ ፈላጊዎችን ወደ ስራ ሊያስገባ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ያፀድቃል፡፡
4. በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች በመስፈርቱ መሰረት መለየታቸውን ማረጋገጥ፣
5. ባሉት የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች በአደረጃጀትና አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
6. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸውን የግዴታ ቅድመ ብድር ቁጠባ እየቆጠቡ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
7. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የወጣቶች፣ ሴቶችና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣
8. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ተሰማርተው ተጠቃሚ የሆኑ አንቀሳቃሾች በተቀመጠው አሰራር መሰረት ወደ መደበኛው ስራ ዕድል ፈጠራ ዘርፎች መሸጋገራቸውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
9. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች በአካባቢና በተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርሱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
10. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአፈጻጸም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ግብረ-መልስ መስጠት፣
11. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የስራ ዕድል ፈጠራውን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል አፈጻጸሙን ይገመግማል፣ ቅሬታዎችን ይፈታል ለሚመለከተው አካል ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት በወቅቱ ያቀርባል፣
12. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን አንቀሳቃሾች ተሞክሮ እንዲቀመር በማድረግ ለሌሎች ተሞክሮውን በማሳየት እንዲሰፋ ያደርጋል፣

# 2.3. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ አይነቶች

እሴት የማይጨመርባቸዉ ከፍተኛ ማሽነሪ የማይጠይቁና በአነስተኛ ደረጃ ሊሰሩ የሚችሉ የስራ መደቦች ለወጣቶች የጥሪት ማፍሪያነት አገልግሎት እንዲውሉ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት መስራትን የሚጠይቅ ሆኖ የጥሪት ማፍሪያ መስኮች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

- በጥሪት ማፍሪያ ዘርፍ የስራ እድል የሚፈጠርባቸው የስራ መስኮች ዝርዝር

1. በኢንዱስትሪ ዘርፍ (ኮንስትራክሽንና ማዕድን) ንዑስ የስራ መስኮች ዝርዝር
   * በባህላዊ መንገድ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ኤሜራልድ ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ሳፋይድ ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ወርቅ ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ፕላቲኒየም ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ታንታለም ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ዩራኒየም ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ዕምነበረድ ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ የዳይመንድ /አልማዝ/ ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ኦፓል ማውጣት
   * በባህላዊ መንገድ ባዛልት ማውጣት
   * የድንጋይ ካባ ማውጣት
   * ገረጋንቲ (selkected materiale) ማውጣት
   * ሸክላ አፈር ማውጣት
   * ቀይ አፈር ማውጣት
   * አሸዋ ማውጣት
   * የወንዝ ጠጠር ማውጣት
   * ኖራ ድንጋይ ማውጣት ሥራ
   * በባህላዊ መንገድ ጨው ማውጣት
   * ግንባታ ማፍረስ ስራ
   * የከርብ ስቶን መጥረብ
   * የኮብል ስቶን መንገድ ጥገና
   * የኮብል ስቶን መጥረብ
   * የኮብል ስቶን ንጣፍ
   * “Retaining wall construction” የጎርፍ የድጋፍ ግንብ ስራ



2. በአገልግሎት ዘርፍ የስራ መስኮች ዝርዝር ደንና የደን ውጤቶች ጥበቃ
   * የጫኝና አውራጅ አገልግሎት
   * የፓርኪንግ አገልግሎት

* የሌሊት መኪና ጥበቃ አገልግሎት
* የታክሲ ተራ ማስከበር አገልግሎት
* መኪና እጥበት አገልግሎት
* የከተማ ጽዳት አገልግሎት
* የመንግስት ተቋም ጽዳት አገልግሎት
* የመንግስት ተቋማት የመዝናኛ አገልግሎት
* ሌሎች ተመሳሳይ የስራ መስኮች



3. በከተማ ግብርና ዘርፍ የስራ መስኮች ዝርዝር
   * አሳ ማስገር
   * እጣንና ሙጫ ማምረት
   * የመንገድ ዳር እና አካፋይ ሳር ተከላ
   * የመንገድ ዳር ዛፎችን መንከባከብ
   * በከተሞች የወንዝ ዳርቻዎችን ማልማት
   * ሌሎች ተመሳሳይ የስራ መስኮች
4. በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በቀጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል
5. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ የሚፈጠር የስራ ዕድል
6. በተጨማሪም የተፈጥሮ መስህብን በመጠቀም የሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች (ለምሳሌ ሃይቅ ዳር አካባቢ፣ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች፣ በመንግስት የተከለሉ ፓርኮች ... የመሳሰሉት) በጥሪት ማፍሪያ የሰራ መስክ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡
7. ከዚህ በተጨማሪ ክልሎች ያላቸውን ሃብት በመለየት የስራ መስክ ሊለዩ ይችላሉ፡፡

# 2.4. በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ዜጎች የአደረጃጀት ሁኔታ

## 2.4.1 የህጋዊ ሰውነት አሰጣጥ

በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚደራጁ ስራ ፈላጊ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ዜጎች ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በሚዘጋጁ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሚፈጸም ነዉ፡፡ የጥሪት ማፍሪያ የስራ ዘርፎች ከባህሪያቸው አንጻር በአድራሻነት የህጋዊ ሰውነት ሰርተፍኬትን መነሻ በማድረግ በንግድ ቢሮዎች የዋና ምዝገባ በማድረግ ወደ መደበኛ ዘርፎች ከተሸጋገሩ በኋላ በንግድ ህጉ መሰረት በተቀመጠው አሰራር መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 2.4.2 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚደራጁ ማህበራት የአባላት ብዛት ሁኔታ፤

በጥሪት ማፍሪያ በአንድ የስራ መስክ የሚደራጁ ማህበር አባላት ቁጥር ቢያንስ 10 ሆኖ እንደ የስራ መስኩ ነባራዊ ሁኔታ የአባላቱ ብዛት ይወሰናል፡፡ ሆኖም በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በቀጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል ተጠቃሚ የሚሆኑ ዜጎች በፕሮጀክቶች አሰራር መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

# 3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአሰራርና ሽግግር

## 3.1 የስራ ትስስር ሂደት

ሀ. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚገኙበት የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ጽ/ቤት የስራ ትስስር ከሚፈጠርባቸው ተቋማት ጋር መግባቢያ ሰነድ የሚፈራረሙ ይሆናል፡፡

ለ. የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተደረጁ ማህበራትን ዝርዝር መረጃ በማደራጀት የስራ ትስስር ወደ ሚፈጥረው አካል በማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ መንግስታዊ ድጋፎችን በማመቻቸት ወደ ስራ እንዲገቡ የሚደረግ ይሆናል፡፡

ሐ. የስራ ትስስሩን የሚፈጥረው አካል ከአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተደራጅተው የሚመጡትን ማህበራትን ተቀብሎ ውል በማስገባት ወደ ስራ እንዲገቡ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ይሆናል፡፡

መ. የስራ ትስስሩ አፈጻጸም የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ኃላፊ/ተወካይ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ስራ ኃላፊ/አስተባባሪ፣ የስራ ትስስር የተፈጠረበት ተቋምና የስራ ትስስር ተጠቃሚዎች ወኪሎች በተገኙበት ተገምግሞ መልካም ተሞክሮዎችን የማስፋትና እጥረቶች ሳይስፋፉ የማስተካከል ስራ ይሰራል፡፡

## 3.2 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ማህበራት የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች

ሀ. የአመለካከትና የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

ለ. ከጥሪት ማፍሪያው የስራ መስክ ተሸጋግረው ወደ መደበኛ ዘርፎች ለመሰማራት አስቀድመው በመረጡት የስራ መስክ የንግድ ስራ እቅድ እንዲያዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ሐ. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ እንደ አግባብነቱ ስራውን ለመጀመር የሚያስችላቸውን የክህሎትና የስራ አመራር ስልጠና አስቀድመው እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ተቋማት ያለምንም ክፍያ ይመቻችላቸዋል፣

መ. በጥሪት ማፍሪያ ወደ ስራ ለሚገቡ ማህበራት ስለ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂና የስራ ፈጠራ ግንዛቤን ማጎልበት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሠ. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች እንደየስራ ባህሪያቸው የስራ ትስስሩን የሚፈጥረው አካልና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በመቀናጀት ማህበራት ስራቸውን ማከናወን የሚያስችላቸው ጊዜያዊ የመስሪያ ቦታ በማቅረብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፣

ረ. ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚዉሉ ማዕድናት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ማህበራት ሃብቱን ለማውጣት ማሽነሪ በሚያስፈልግበት ወቅት መንግስት በኪራይ መልክ ለማህበራቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

ሰ. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ማህበራት አስፈላጊውን የገበያ ትስስር ድጋፍ ይደረግላቸዋል

ሸ. በጥሪት ማፍሪያ የተሰማሩ ማህበራት በየወቅቱ ከሚያገኙት ገቢ ሽግግር በሚያደርጉበት የስራ መስክ በተዘጋጀው የንግድ ስራ እቅድ መሰረት የውዴታ ግዴታ ቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፣

ቀ. ገቢያቸዉንና ወጪያቸውን በአግባቡ እንዲመዘግቡና እንዲይዙ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፣

በ. በጥሪት ማፍሪያ የተሰማሩ ማህበራት በተሰማሩበት ስራ መስክ ስርዓትን አክብረው እንዲሰሩ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል።

ተ. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ ውጤታማ የሆኑ ማህበራት ህጋዊነታቸው በጠበቀ አግባብ ወደ መደበኛዉ የስራ ዕድል ፈጠራ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፣

## 3.3 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ማህበራት ቆይታ ጊዜ

በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ማህበራት ከሚያገኙት ገቢ ቆጥበው ወደ መደበኛ የስራ አማራጮች መሰማራት ለማይችሉ ሰዎች ሃብት አፍርተው ወደ መደበኛ የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ለማድረግ እና ሌሎች መነሻ ካፒታል ለሌላቸው ስራ ፈላጊ ዜጎች በማስተላለፍ የሽግግር ሂደቱ ወጥና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የጸዳ እንዲሆን ለማስቻል በየዘርፉ እና በስራ መስኩ የቆይታ ጊዜያቸውን እና የአሰራር ሁኔታዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።





### 3.3.1 በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ማህበራት ቆይታ ጊዜ

| የስራ ዘርፍ | የስራ መስክ | የቆይታ ጊዜ ጣሪያ | በንግድ ስራ ዕቅድ 20 በመቶ ቁጠባ መጠን |
|---|---|---|---|
| 1. ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኮንስትራክሽንና ማዕድን ንዑስ የስራ መስኮች | በባህላዊ መንገድ ማዕድን ማውጣት | 1 አመት ከ6 ወር | በጊዜ ገደብ ቆይታቸው ቀድሞ ማህበራቱ ቅድሚያ ባዘጋጁት የንግድ ስራ እቅድ 20 በመቶ በሚሟላ ጊዜ የሚሸጋገሩ ይሆናል። |
| | የድንጋይ ካባ ማውጣት | 1 አመት | |
| | ሸክላ አፈር ማውጣት | 2 አመት | |
| | ቀይ አፈር ማውጣት/ አሸዋ ማውጣት | 1 አመት | |
| | ላይም ስቶን እና ኖራ ድንጋይ ማውጣት ሥራ | 1 አመት | |
| | ጨው ማውጣት | 1 አመት | |
| 2. በአገልግሎት | ግንባታ ማፍረስ ስራ | 2 አመት | |
| | የከርብ ስቶን/ የኮብልስቶን መጥረብ | 1 አመት | |
| | የኮብልስቶን ንጣፍ | 1 አመት | |
| | የኮብል ስቶን መንገድ ጥገና | 1 አመት | |
| | የድጋፍ ግንብ ስራ/ "Retaining wall construction" የጎርፍ | 1 አመት | |
| | ደንና የደን ውጤቶች ጥበቃ | 2 አመት | |
| | የጫኝና አውራጅ አገልግሎት | 2 አመት | |
| | የፓርኪንግ አገልግሎት | 2 አመት | |
| | የሌሊት መኪና ጥበቃ አገልግሎት | 2 አመት | |
| | የታክሲ ተራ ማስከበር አገልግሎት | 1 አመት ከ6 ወር | |
| | መኪና እጥበት አገልግሎት | 2 አመት | |
| | የከተማ ጽዳት አገልግሎት | 2 አመት | |
| | የመንግስት ተቋም ጽዳት አገልግሎት | 2 አመት | |
| 3. በከተማ ግብርና | አሳ ማስገር | 2 አመት | |
| | እጣን ማምረት | 2 አመት | |
| | የመንገድ ዳር እና አካፋይ ሳር ተከላ | 2 አመት | |
| | የመንገድ ዳር ዛፎችን መንከባከብ | 2 አመት | |
| | በፓርኮች አካባቢ ሳሮችን በማጨድ ለእንስሳት መኖ ግብዓት ማቅረብ | 2 አመት | |
| | በከተሞች የወንዝ ዳርቻዎችን ማልማት | 2 አመት | |

### የቆይታ ጊዜው አፈጻጸም

1. በስራ ዘርፉ የሚሰማሩ ማህበራት በስራ መስኩ ላይ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ጣሪያ በ3.3.1 ላይ እንደተቀመጠው ሆኖ በቅደሚያ ወደሚሸጋሩበት የስራ መስክ ባዘጋጁት የንግድ ስራ ዕቅድ ካፒታል 20 በመቶውን በሚሟላበት ወቅት የቆይታ ጊዜው በቁጠባ መጠኑ የሚወሰን መሆኑን በሚገቡት ውል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. ይህ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተቀመጠውን የአሰራር ደንብ በመተላለፍ የሚሰናበቱትን አይመለከትም፣

3. በስራ ዘርፉ የተሰማሩ ማህበራት በተሰማሩበት የስራ መስክ በገቡት የስራ ውል መሰረት ግዴታቸውን የማይወጡና የአሰራር ችግር የፈጠሩ ከሆነ የቆይታ ጊዜ ጣሪያዉ ያልተጠናቀቀ ቢሆንም የስራ ውላቸው የሚቋረጥ ይሆናል፣

4. በዚህ ጋይድላይን መሠረት መስፈርቶችን አሟልተው ከሚገቡ ማህበራት በፊት በጥሪት ማፍሪያው ቦታ እየተገለገሉ የቆዩ ማህበራትን በተመለከተ በከተማ/በወረዳው የጥሪት ማፍሪያ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ማህበራቱ ያሉበትን ደረጃ በመገምገም ወደ ሌላ ዘርፍ እንዲሸጋገሩ ወይም ተጨማሪ የቆይታ የጊዜ ውል እንዲገቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በጥሪት ማፍሪያነት በጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ እንደየፕሮጀክቱ ተጨባጭ ሁኔታ በአካባቢው በሚገኙ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አማካኝነት እንዲቆጥቡ በማድረግ ለሚሸጋገሩበት የስራ ዘርፍ ቅድመ ብድር ቁጠባ መጠን እንዳሟሉ የሚሸጋገሩ ይሆናል፡፡

## 3.4 ከጥሪት ማፍሪያ የስራ ዘርፎች ወደ መደበኛ የሚሸጋገሩበት ሁኔታ

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ አማራጮች ተጠቃሚ የሆኑ ማህበራት የመውጫ ጊዜ በተራ ቁጥር 3.3.1 በተጠቀሰው መሰረት ይሆናል፣

2. ተጠቃሚ ማህበራት ባዘጋጁት የአዋጭነት የንግድ ስራ እቅድ መሰረት ወደ ስራ እንዲገቡ አስፈላጊ ድጋፎች ይመቻቻሉ፣

3. የመደበኛ አደረጃጀት አማራጮችን በመጠቀም ወደ ስራ የሚገቡ ማህበራት ከጥሪት ማፍሪያ ተሸጋግረው የወጡና ተገቢውን ዕውቅና ያገኙ ማህበራት ይሆናሉ፣

4. ከጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ወደ መደበኛዉ የስራ ዕድል ለመሰማራት የንግድ እቅዱ የሚጠይቀውን የመነሻ ካፒታል 20 በመቶ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ ይህን የመነሻ ካፒታል ፍላጎት ለማሟላት ማህበሩ በየጊዜው ከሚያገኘዉ ገቢ 30 በመቶ የሚሆነውን ገንዘብ ወደ አነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፣

5. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ የተሰማሩ ማህበራት መንግስታዊና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በየጊዜው በሚያደርጉት የገበያ ትስስር መሰረት ክፍያ ሲፈጽሙ 30 በመቶውን የግደታ ቁጠባ በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት በማህበሩ ስም ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ይህ ገንዘብ በሚፈለገው መንገድ ገቢ እየተደረገ መሆኑን በዋናነት አነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋም፣ የአንድ ማእከል አገልግሎትና የጥሪት ማፍሪያ ፕሮጀክቱን የሚመራው አካል አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

6. ከጥሪት ማፍሪያ ፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜያቸውን አጠናቀው ሲወጡ ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ከመሸጋገራቸው በፊት ስለህጋዊነት ማስፈንና መንግስታዊ ድጋፎች አሰጣጥ በተከታታይነት ግንዛቤ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

7. የማህበሩ አባላት ሽግግር አድርገው ለሚሰማሩበት የስራ መስክ አስፈላጊውን ስልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል። ስልጠናውን በአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚመቻች እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የሚሰጥ ይሆናል፣

8. በጥሪት ማፍሪያነት ስራ መስክ የተሰጠውን ጊዜያዊ የአደረጃጀት ሴርተፍኬት በመመለስ ወደ መደበኛ የስራ ዕድል ፈጠራ ይሸጋገራል፣

9. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ቆይተው የተሻለ ሃብት መፍጠር ከቻሉ በመረጡት የእድገት ተኮር ዘርፎች መሰማራት እንዲችሉ የምክርና መረጃ ድጋፍ እንዲሁም የመንግስትን አቅም ባገናዘበ መልኩ የህጋዊነት ማስፈንና የመንግስታዊ ድጋፎች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

10. የቆይታ ጊዜያቸውን ሳይጨርሱ የመሸጋገሪያ መስፈርቱን አሟልተው ከጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሚሸጋገሩ ማህበራት የሚያስፈልጋቸው ህጋዊነት የማስፈንና መንግስታዊ ድጋፎች ይደረጋል፣

# 3.5 በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚደራጁ ማህበራት መብትና ግዴታ

## 3.5.1 የማህበራቱ መብት

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ተደራጅተው ወደ ስራ የገቡ ማህበራት ስራውን ሊያሰራ የሚችል የክህሎትና የአመለካከት ስልጠና፤ የገበያ ትስስር፣ የቁጠባ አገልግሎት፣ የእለት ገቢና ወጪ መዝገብ አያያዝ ድጋፎችን የማግኘት፤

2. ለጥሪት ማፍሪያነት በተሰጣቸው ቦታ የመስራት፤

3. ማንኛውም በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማራ ማህበር 20 ከመቶው ቅድመ ብድር ቁጠባ ጥሪት ማፍራቱ ሲረጋገጥ ወደ መደበኛ ዘርፍ የመሸጋገር መብት ይኖረዋል።

## 3.5.2 የማህበራቱ ግዴታዎች

1. ማንኛውም በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማሩ ሁሉም የማህበሩ አባላት ለመስራት በገቡት ውል መሠረት በግንባር በመገኘት ሙሉ የስራ ስዓታቸውን ስራ ላይ የማዋል፤

2. የተሰጣቸውን ማናቸውም የመንግስት ድጋፍ (የመስሪያ ቦታ፣ የገበያ ዕድል፣ የስራ መሳሪያ፣ ወዘተ...) ወይም ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለ3ኛ ወገን አሳልፎ አለመስጠት፤

3. ማንኛውም በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማሩ ማህበራት የሚሰሩት ስራ ጥራቱን የጠበቀ መሆን ይኖርበታል፣

4. የማህበራቱ አባላት የሥራ ሥነ-ምግባር ሊኖራቸው ይገባል፣

5. ማንኛውም ማህበር በውል ለማስረከብ በገባው የስራ ውል መሰረት የመስሪያ ቦታውን ማስረከብ፣
6. ማንኛውም ማህበር በየጊዜው በማህበሩ ስም ከሚያገኘው ገቢ በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የቁጠባ ሂሣብ በመክፈት ከገቢው 30 በመቶ የግዴታ ቁጠባ የመቆጠብ፣
7. የቴክኒክም ሆነ የአመለካከት ስልጠናዎችን በሚሰጥበት ጊዜ የመከታታል፣
8. በጎደለ የማህበሩ አባላት ቀጥሮ አለማሰራት፣
9. የጎደለ የማህበር አባል ለአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በወቅቱ የማሳወቅ፣
10. ማህበሩ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የቆይታ ጊዜውና በተዘጋጀው የአዋጭነት የንግድ ስራ እቅድ መሰረት 20 በመቶ ሲቆጥብ የመሸጋገር፣
11. በተሰማሩበት የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሌላ ተግባር የሚፈለግ ከሆነ ቦታውን የማስረከብ፤
12. በጥሪት ማፍሪያ የተሰማሩ ማህበራት በውል ከተሰጣቸው የመስሪያ ቦታ ውጪ ያለመስራት፣
13. በአባላቱ መካከል መልካም የሆነ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ መደጋገፍ ችግር የታየባቸውም እንዲታረሙ ማድረግ፣
14. ስለሚሰሩት ስራ ጥራትና የአባላቶቹ የአሰራር ሂደት በየሳምንቱ መገምገም፣
15. ማህበራቱ የሚመለከታቸው ሃብቱን የሚያስተዳድሩ ተቋማት በሚያወጡት መመሪያ መሰረት የአካባቢና የተፈጥሮ ሃብቶችን የመጠበቅና የመንከባከብ መልሰው የማልማት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል።
16. ማንኛውም በጥሪት ማፍሪያ ስራ የተሰማራ ማህበር በተሰማራበት የስራ መስክ የተቀመጠለትን ግዴታ ያልተወጣና ደንብ የተላለፈ እንደሆነ በውሉ ላይ በገባው የስራ ግዴታ መሰረት የቆይታ ጊዜ ባይጠናቀቅም የስራ ውሉ ይቋረጣል፣

# ክፍል አራት

# 4. የፈፃሚና የባለ ድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ለወጣቶች በጥሪት ማፍሪያ የሚያገለግሉ የስራ መስኮች በሚመለከታቸዉ ተቋማት ተለይተዉ አገልግሎት ላይ እንዲዉሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ህጎችን በማጥናትና ለመንግስት በማቅረብና ሲፈቀድም ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ፣
2. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ልየታና የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊ ዜጎች ተለይተው እንዲሳተፉና መነሻ ካፒታል ማፍራት የቻሉ ዜጎች ወደ መደበኛው አደረጃጀት እንዲገቡ የማድረግ ተግባራትን ከተሞች እንዲደግፉ እና እንዲፈጽሙ ይመራል፣ ያስተባብራል፣
3. በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተማ ሴክተር ላይ ለጥሪት ማፍሪያነት የሚያገለግሉ የስራ መስኮች እንዲለዩና  የህግ ማእቀፍ እንዲዘጋጅላቸው ያደረጋል፣
4. በጥሪት ማፍሪያ ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በየደረጃው እንዲያሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
5. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ልየታ፣ በስራ መስኩ የተሰማሩ ማህበራት የቆይታ ጊዜና የሽግግር ሁኔታ አስመልክቶ ለክልልና ከተማ አስተዳደሮች የአቅም ግንባታ ስራዎች ያከናውናል፣
6. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተፈጠረዉን የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በስድስት ወር እና በየዓመቱ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል።

## 2. በየደረጃው የሚገኙ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት፣

1. በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤቶች አባል ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣
2. በየአካባቢው በጥሪት ማፍሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ የስራ መስኮች ተለይተው መያዛቸውን ያረጋግጣል፤ ለጥሪት ማፍሪያነት ሊውሉ የሚችሉ የስራ መስኮችን በመወሰን አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣
3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ ማህበራት አስፈላጊ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
4. በጥሪት ማፍሪያነት የተለዩ የስራ መስኮች ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችላቸውን የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች  እየተሰጠ መሆኑን ክትትል ያደረጋል።
5. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተደራጁ ማህበራት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ወደ መደበኛ  የስራ ዘርፎች እየተሸጋገሩ መሆናቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

6. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለማሰማራት በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

## 3. የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

1. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች አደረጃጀትና የአሰራር ሁኔታ የሚመራበትን ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
2. የዘርፉን የክልል /የከተማ አስተዳደሮችን አቅም ይገነባል፣
3. የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ልየታ፣ የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች ልየታና ወደ መደበኛ የእድገት ተኮር ዘርፎች የሚደረግውን የሽግግር ሁኔታ በተቀመጠው መሰረት እንዲፈጸም ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
4. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች አደረጃጀትና የአሰራር ሁኔታ ዙሪያ ችግሮችን ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችል ጥናቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ያከናውናል መድረኮችን በመፍጠር በውይይት እንዲዳብሩ እና እንዲጎለብቱ ያደርጋል፣
5. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚሰማሩ ዜጎችን ልየታ፣ የተደራጁ ማህበራት እና የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች መረጃዎችን በአግባቡ እንዲደራጅ ይደግፋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
6. በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክት የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የጋራ ዕቅድ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ተወካይ ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያስጸድቃል፣
7. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች ግዙፍ ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አካባቢ ከሚገኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተመልምለው በፕሮጀክቶቹ የስራ ዕድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን በክትትልና ድጋፍ ያረጋግጣል፣
8. በጥሪት ማፍሪያው የስራ መስክ ተሰማርተው ሃብት ያፈሩ ማህበራት ወደ እድገት ተኮር ዘርፎች እንዲሸጋገሩ ከማድረግ አንጻር የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመለየት በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈቱ ያደርጋል፣
9. በጥሪት ማፍሪያ ለተሰማሩ ማህበራት በየስራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፣
10. የቁጠባ ባህል ለማዳበር ከሚያገኙት ገቢ የሚቆጥቡበትን አሰራር በመዘርጋት፣ በዚህ ዘርፍ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ መደበኛ የስራ ዘርፎች ለመሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል መደረጉን ያረጋግጣል፣
11. ከአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እስከ ቢሮ/ኤጀንሲ ለክትትልና ቁጥጥር አመችነት ይኖረው ዘንድ የተቀናጀ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
12. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ያለውን አፈጻጸም ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ለዘርፉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስገመግማል፣ የተደረሰበትን የጋራ ስምምነት አፈፃፀም ይከታተላል፡፡

## 4. በየደረጃው የሚገኙ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር/ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. ለጥሪት ማፍሪያነት የሚያገለግሉ በባህላዊ መንገድ ማዕድን ልማት የሚደረግባቸውን ቦታዎች ተለይቶ ከተከለለ በኋላ ለተጠቃሚዎች መተላለፉን ያረጋግጣል፤ በልማት ወቅት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
2. በማዕድን ዘርፍ የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል የሚፈጥሩ የስራ መስኮችን በመለየት በዕቅዱ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
3. በባህላዊ መንገድ ማዕድን ልማት በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች በተፈጠረው የስራ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸውን ክትትል ያደርጋል፣
4. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ያለውን የስራ እድል ፈጠራን አስመልክቶ የሚፈጠሩ የተለያዩ ማነቆዎችን በመለየት ከስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር በመሆን ለበላይ አመራሩ በማቅረብ እንዲፈቱ ያደርጋል፣
5. ለስራ ወደ ሳይቶች ለሚሰማሩ የማህበር አባላት የማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
6. የባህላዊና አነስተኛ ማእድን ልማት የስራ መስኮች የስራ እድል መፍጠሪያ በመሆን የቅድመ ካፒታል አቅም መፍጠሪያ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች ማነቆ የሆኑባቸውን የአሰራር ስርዓቶች በመለየት በመመሪያ እንዲፈቱ ያደርጋል፣
7. በጥሪት ማፍሪያ ስራ ተደራጅተው አቅም ያጎለበቱትን ወደ መደበኛ የስራ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

## 5. በየደረጃው ያሉ የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር/ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊ ሴቶችን እና ወጣቶችን በመለየት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ እንዲመዘገቡ ግንዛቤ በመፍጠር አፈጻጸሙን ክትትል ያደርጋል፣
2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች መሰማራት ያለባቸው ስራ ፈላጊ ሴቶችን እና ወጣቶችን የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ከዘርፉ አስፈፃሚዎች ጋር የጋራ ዕቀድ ያዘጋጃል ይተገብራል፣
3. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊ ሴቶች እና ወጣቶች ልየታ፣ አደረጃጀትና የስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ የሴቶች አደረጃጀቶችን (ማህበር፣ ፎርምና ፌደሬሽን) አቅም በመገንባት ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣
4. በጥሪት ማፍሪያው የስራ መስክ በሴቶች እና በወጣቶች የሚመሩ ማህበራትን የመደገፍ የመከታተልና የማበረታታት ስራ ያከናውናል፣

5. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ሴቶች እና በወጣቶች በስራ ፈላጊዎች ልየታ፣ አደረጃጀት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ይሰጣል።

## 6. በየደረጃው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተግባርና ሀላፊነት፣

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለመሰማራት የተመለመሉ ስራ ፈላጊዎችን ስራውን ለመጀመር የሚያስችላቸውን እውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ የቴክኒክ ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው የስራ መስኮች አሰፈላጊውን ስልጠና ይሰጣል፣

2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለመሰማራት የተመለመሉ ስራ ፈላጊዎችን የአመለካከት ስልጠና እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ስልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል፣

3. ስልጠና የሚሰጥባቸውን የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች በመለየት በስልጠና ፕሮግራም እንዲካተቱ ያደርጋል፣

4. የማህበሩ አባላት ወደ መደበኛ ዘርፎች ሽግግር አድረገው ለሚሰማሩበት የስራ መስክ አሰፈላጊውን የክህሎት ስልጠና ይሰጣል።

5. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በየደረጃው የሚያስተባብሩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት፣

6. ከፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር በመሆን በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት ዙሪያ የጋራ ዕቅድ አዘጋጅቶ መፈራረም፣

7. በጥሪት ማፍሪያ የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች ግዙፍ ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አካባቢ ከሚገኙ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተመልምለው በፕሮጀክቶቹ የስራ ዕድል እየተፈጠረላቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ፣

8. በየፕሮጀክቱ 20 በመቶ በመቆጠብ ወደ መደበኛ ዘርፎች መሸጋገር ያለባቸውን ማህበራት መረጃ በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ማሰራጨት፣

9. በጥሪት ማፍሪያነት በተመረጡ የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች በስራ ዕድል ፈጠራው ላይ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመለየት መፍታት፣

10. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎች በየስራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፣

11. የቁጠባ ባህል ለማዳበር የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እና ከአነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሚቆጥቡበትን አሰራር መዘርጋት፣ በዚህ ዘርፍ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ መደበኛ ዘርፍ መሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

12. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተፈጠረዉን የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ፣ በስድስት ወር እና በየዓመቱ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል።

## 7. የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት፤

1. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ ማህበራት የግዴታ ቁጠባ እና የፈቃደኝነት ቁጠባ እንዲቆጥቡ ይቀሰቅሳል፣ ያስተምራል፣ ምክር ይሰጣል፤
2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማሩ ማህበራት በየጊዜው ከሚያገኙት ገቢ የግዴታ ቁጠባ 30% እንዲቆጥቡ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ማህበራት የቁጠባ አገልግሎት ይሰጣል፤

## 8. በየደረጃው የሚገኙ ትራንስፖርት ሚኒስቴር/ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት፤

1. የትራንስፖርት ዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሳለጥ የሚረዱና ለጥሪት ማፍሪያነት የሚውሉ የስራ መስኮችን ይለያል፤
2. በተለዩት የስራ መስኮች መሰረት የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊዎች ከአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጋር በመነጋገር እንዲለዩ ያደርጋል፣ ወደስራ እንዲገቡ በቅንጅት ይሰራል፤
3. የቁጠባ ባህል ለማዳበር የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎች እና ከአነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሚቆጥቡበትን አሰራር ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ በተሰማሩበት የስራ መስክ የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ መደበኛ ዘርፍ መሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
4. በትራንስፖርት ዘርፉ አገልግሎት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለስራ ፈላጊዎች የስራ እድል ከመፍጠር አንጻር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፤ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
5. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ ለማይችሉ ስራ ፈላጊዎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በየወሩ፤ በየሩብ አመቱ፤ በስድስት ወር እና በየዓመቱ ይገመግማል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል::

## 9. በየደረጃው የሚገኙ ግብርና ሚኒስቴር/ቢሮ/ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት፤

1. በየደረጃዉ ከሚገኙ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ተቋማት ጋር በመሆን በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮችን በመለየት ስራ ፈላጊዎችን ወደ ስራ ለማስገባት የሚያስችል የጋራ ዕቅድ ያዘጋጃል፤
2. በዘርፉ ለጥሪት ማፍሪያነት የሚያገለግሉ የስራ መስኮችን ወይም ፀጋዎችን ይለያል፤
3. በተለዩ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ከአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጋር በመነጋገር የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊዎች ወደ ስራ እንዲገቡና ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
4. የቁጠባ ባህል ለማዳበር የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መሰጫ ጣቢያዎች እና ከአነስተኛ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሚቆጥቡበትን አሰራር መዘርጋት፤ በእነዚህ የስራ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ማህበራት የሚያገኙትን ጥሪት ይዘው ወደ መደበኛ ዘርፍ መሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
5. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተፈጠሩ የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በየወሩ፤ በየሩብ አመቱ፤ በስድስት ወር እና በየዓመቱ ይገመግማል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል::

## 10. የክልል/የዞን/የከተማ/የወረዳ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. የክልሉ /የዞኑ/የከተማ/ የወረዳ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ተቋማት ከባለድርሻ አካላት እና ከተለያዩ የህዝብ አደረጃጀቶች ጋር በመቀናጀት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎችን በዚህ ጋይድላይን በተቀመጠው መስፈርት መሠረት እንዲመለመሉ፣ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ በአሰራር ስርዓቱ መሰረት እንዲደራጁ የዕውቀት ክህሎት ስልጠና፤ የገበያ ወይም የስራ ትስስር እና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
2. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎችና የተሰማሩ ማህበራት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመከታተል ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ችግሩ እንዲፈታ በበላይነት ያስተባብራል፣
3. በዚህ ጋይድ ላይን በተቀመጠው መሠረት መሸጋገር የሚፈልጉትን እና የሽግግር ጊዜያቸው የደረሰ ማህበራት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ወደ መደበኛ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ የማደራጀት፤ እንደአስፈላጊነቱ የመስሪያና መሸጫ ቦታ ድጋፍ፣ የስልጠናና የገበያ ትስስር እንዲሁም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፎች ቅድሚያ እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

## 11. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. በአካባቢ ያሉ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይለያል፣
2. ከተለያዩ የህዝብ አደረጃጀቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ላይ የሚሰማሩ ስራ ፈላጊዎችን ይመለምላል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ በጋይድ ላይኑ መሰረት ያደራጃል፣ ስልጠናና የስራ ትስስር እንዲያገኙ ያመቻቻል፣
3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ተጠቃሚዎች የውዴታ እና የግዴታ ቁጠባ እንዲቆጥቡ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተከታታይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ያስፈጽማል፣
4. በጥሪት ማፍሪያ ዘርፍ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ማህበራት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በመለየትና በመከታተል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩ የሚፈታበትን አግባብ ያመቻቻል፣
5. በዚህ ጋይድላይን በተቀመጠው መሰረት ወደ መደበኛ ዘርፎች መሸጋጋር የሚፈልጉትንና የቆይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ማህበራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፋላጊውን ድጋፍ ቅድሚያ እንዲያገኙ ያመቻቻል፣
6. በአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አካባቢ በሚገኙ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚገኙ ማህበራት መጀመሪያ የነበሩበት ሁኔታና የተገኙ ለውጦችን በሚያሳይ መልኩ ዝርዝር መረጃ ያዘጋጃል፣
7. የቅድመ ብድር ቁጠባ መቆጠብ የማይችሉ ስራ ፈላጊዎች በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ የስራ ዕድል ፈጠራ አፈጻጸም በየወሩ፣ በየሩብ አመቱ፣ በስድስት ወር እና በየዓመቱ ስራውን ይገመግማል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል።

# ክፍል አምስት

## 5. ክትትልና ድጋፍ፣ ግብረ መልስ

* በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተደራጁ ማህበራት በየደረጃው የተደረጉ ድጋፎች፣ በየጊዜው የተገኙ መሻሻሎችና ለውጦች በየወሩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በየሩብ ዓመቱ በእያንዳንዱ ማህበር መረጃው በስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ይመዘገባል።
* ማህበራቱ በራሳቸው ነፃነት መንቀሳቀሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ እስኪሸጋገሩ ድረስ አጠቃላይ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
* ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እስከ ቢሮ /ኤጀንሲ ለክትትልና ቁጥጥር አመችነት ይኖረው ዘንድ የተቀናጀ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ይደረጋል፣
* በአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አካባቢ በሚገኙ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የሚገኙ ማህበራት በመጀመሪያ የነበሩበትን ሁኔታና የተገኙ ለውጦችን በሚያሳይ መልኩ ዝርዝር መረጃ ይዘጋጃል፣
* በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የተሰማሩ ማህበራት ውጤታማነት የኤጀንሲው ወይም ቢሮ በየ3 ወር፣ ከተሞች በየወሩ ክትትልና ግምገማ ማከናወን ይኖርባቸዋል። ነገር ግን በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ያሉ ባለሙያዎች በቅርበት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በሳምንት አንድ ጊዜ በአጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴዎች ግምገማ ማከናወን፣ ..
* የግምገማ ሂደቱ በመስክ ጉብኝት በማድረግ ለተከሰቱ ችግሮች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠትና የታዩ ጉድለቶች ለባለ ድርሻ አካላት በግብረ መልስ እንዲያሳውቁት ይደረጋል።

# ክፍል ስድስት

## 6. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአደረጃጀትና አሰራር ጋይድ ላይን በከተሞች የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ በክልሎች እና በፌደራል ከተማ አስተዳደሮች ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል።

# ክፍል ሰባት

## 7. ጋይድ ላይኑን ስለማሻሻል

ይህ ጋይድ ላይን እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ካቢኔ/ መስተዳድር ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል፡፡

# ክፍል ስምንት

## 8. ጋይድ ላይኑ ስለሚጸናበት ሁኔታ

ይህ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች የአደረጃጀትና አሰራር ጋይድ ላይን በልዩ ሁኔታ በክልሉ ካቢኔ/ መስተዳደር ምክር ቤት ታይቶ ከፀደቀበት ከዛሬ ______ ቀን ________ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ማህበራት ውል ማስገቢያ ሰነድ

### 1. የውሉ ዓላማ (ይዘት)

በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚሰማሩ ዜጎች ከኪራይ ሰብሳቢነት በፀዳ መልኩ ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ መነሻ ካፒታል አፍርተውና ወደ መደበኛ የስራ ዕድል ፈጠራ እስኪሸጋገሩ በስራ ቆይታቸው ላይ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ፣ ያላቸውን መብትና የቆይታ ጊዜ የሚወስንበትን ነው፡፡

### 2. በየአካባቢው የተለዩ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የሚሰሩ ስራዎች

በጥሪት ማፍሪያነት የተለዩ የስራ መስኮች እና ቦታዎች የሚሰሩ ስራዎች በጥሪት ማፍሪያ የአደረጃጀትና አሰራር ጋይድ ላይን መሰረት ይሆናል፡፡

### 3 ስለ ውል፣ መብትና ግዴታ

#### 3.1. ውል

ውል ሰጪ

በዚህ ክፍል በተዘጋጀው የውል ሰነድ ውል ሰጪ ----- ክልል /ከተማ አስተዳደር የሚገኝ የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስኩን የሚያስተዳድረው------------- ቢሮ /ጽ /ቤት ሲሆን ማህበር ስያሜ-------------------------------

የማህበሩ አባላት መረጃ

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | ክልል/ ከተማ አስተዳደር | ከተማ/ ዞን | አድራሻ | | | | በማህበሩ ያለዉ ኃላፍነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ክ/ከተማ | ቀበሌ/ ወረዳ | የቤት ቁጥር | ስልክ ቁጥር | |
| 1 | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | | | |

ውል ተቀባይ ደግሞ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተደራጀዉ --------------- የሚባል ማህበር ይሆናል፡፡ ውሉም ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

እኛ ስማችን ከዚህ በላይ የተዘረዘርነው ስራ ፈላጊዎች

በቀን --------------- ዓ.ም በ------- ክልል/ከተማ አስተዳደር በ----------ዞን/ከተማ ------------ ክ/ከተማ ወረዳ --------------- የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ----------------------------------------- የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ --------------------------- በሚል የማህበር ስም በ ------------------------------ (የጥሪት ማፍሪያ) የስራ መስክ ተደራጅተን ለመስራት ---------------- ከተማ/ክ/ከተማ/ወረዳ/ አስተዳደር ውስጥ ልዩ ስሙ ------------------- በተባለ አካባቢ የተሰጠንን ----------------- ቦታ ስንረከብ በቦታው ላይ የምንሰራው ከተረከብንበት ጊዜ ጀምሮ ለ-------- ዓመት ሲሆን ከዚህ በታች የተገለጸውን መብታችንና ግዴታችንን ተረድተን ለመፈጸም ተዋውለናል።

# 3.2 መብትና ግዴታዎች

## 3.2.1 የውል ሰጪ መብትና ግዴታዎች

ሀ. የውል ሰጪ መብት

1. ማህበራቱ በገቡት ውል መሰረት ተግባር ላይ መሆናቸውን መከታተል፣
2. ማህበራት የውል ዘመናቸው ሲጠናቀቅና የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ ደንቡን በሚተላለፉ ጊዜ ውል ማቋረጥ፣
3. ቦታው በልማት በሚፈለግበት ወቅት ለማህበራቱ በማሳወቅ ማስለቀቅ።

ለ. የውል ሰጪ ግዴታዎች

1. በጥሪት ማፍሪያ የተሰማሩ ማህበራት ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጋር በመቀናጀት ፈጥኖ ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣
2. ማህበራቱ ከሚያገኙት ገቢ 30 በመቶ በማስቆጠብ ወደ መደበኛ ዘርፎች መሸጋገር ያለባቸውን ማህበራት መረጃ በማሰባሰብ ለሚመለከተው አካል ማስራጨት፣
3. በጥሪት ማፍሪያነት የተሰማሩ ማህበራት የሚያጋጥማቸውን ማነቆዎችን በመለየት መፍታት፣
4. ለማህበራት በየስራ መስካቸው የሚኖርባቸውን የቴክኒክና የግንዛቤ ክፍተት አጥንቶ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት።

## 3.2.2 የውል ተቀባይ መብትና ግዴታዎች

ሀ. የውል ተቀባይ መብት

1. በተሰጠው ቦታ ላይ በተፈቀደለት የስራ መስክ ሰርቶ የመለወጥ፣
2. በጥሪት ማፍሪያ አደረጃጀትና አሰራር ጋይድ ላይን መሰረት የሚሰጡ ድጋፎችን የመጠየቅ እና የማግኘት፣
3. አባል ሲጎደል ለጽ/ቤቱ በማሳወቅ መስፈርቱን የሚያሟላ አባል መተካት

## ለ. የውል ተቀባይ ግዴታ

1. ማንኛውም በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የተሰማሩ ሁሉም የማህበሩ አባላት ለመስራት በገቡት ውል መሠረት በግንባር በመገኘት ሙሉ የስራ ስዓታቸውን ስራ ላይ የማዋል፣
2. የተሰጣቸውን ማናቸውም የመንግስት ድጋፍ ወይም ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ለ3ኛ ወገን አሳልፎ አለመስጠት፣
3. በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ላይ የተሠማሩ ማህበራት ለመሥሪያ የተሰጣቸውን ቦታ በማንኛውም ሁኔታ ለ3ኛ ወገን አለማስተላለፍ፣
4. ማንኛውም ማህበር በየጊዜው በማህበሩ ስም ከሚያገኘው ገቢ በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የቁጠባ ሂሣብ በመክፈት በከፈተው ሂሳብ ከገቢው 30% የግዴታ ቁጠባ መቆጠብ፣
5. የማህበሩ አባላት የቴክኒክም ሆነ የአመለካከት ስልጠናዎችን በሚሰጥበት ጊዜ የመከታተል፣
6. በጎደለ የማህበሩ አባላት ቀጥሮ አለማሰራት፣
7. የጎደለ የማህበር አባል ለአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ በወቅቱ የማሳወቅ፣
8. በተሰማሩበት የጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ ለሌላ ተግባር የሚፈለግ ከሆነ ቦታውን የማስረከብ፣
9. በጥሪት ማፍሪያ የተሰማሩ ማህበራት በውሉ ከተሰጣቸው የመስሪያ ቦታ ውጪ ያለመስራት፣
10. ማህበራቱ የአካባቢና የተፈጥሮ ሃብቶችን የመጠበቅና የመንከባከብ፣
11. ማህበሩ በተሰጠው ቦታ ላይ ምንም ዓይነት ግንባታ ያለመገንባት፣
12. ቦታውን ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ስራ መጀመር፣
13. ማህበሩ በጥሪት ማፍሪያ የስራ መስክ የቆይታ ጊዜውና በተዘጋጀው የአዋጭነት የንግድ ስራ እቅድ መሰረት 20% ቁጠባ መጠን በሚሟላበት ጊዜ ወደ መደበኛ ዘርፍ መሸጋገርና ቦታውን ማስረከብ።

# 3.3 ውሉ የሚቋረጥባቸው ወይም የሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ይህ ውል በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣል ወይም ይፈርሳል፡-

1. የውሉ ዘመን ሲያበቃ ፣
2. ውል ተቀባይ በዚህ ውል የተመለከቱ ግዴታዎችን ሳያስፈፅም በመቅረቱ ምክንያት፣
3. ውል ተቀባይ ከውል ዘመኑ አስቀድሞ በንግድ ስራ ዕቅዱ መሰረት የመነሻ ካፒታል የሚሆነውን 20 በመቶ ቁጠባ የሚሟላ ከሆነ፣
4. በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1792 እና 1793 በተጠቀሰው መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ውሉ ይቋረጣል፡፡

ይህ ውል ሰጪ እና ውል ተቀባይ ተስማምተው ከተዋዋሉበት ከ ------------------- --------ዓ. ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የውል ሰጪ

| የውል ሰጪ የጽቤቱ ሃላፊ/ተወካይ | የውል ተቀባይ /የማህበሩ ሰብሳቢ/ |
|---|---|
| ስም ------------------------------ | ስም ---------------------- |
| ፊርማ --------------------------- | ፊርማ ---------------------- |
| ቀን ---------------------------- | ቀን ----------------------- |

እማኞች

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1ኛ. | ------------------------------- | ------------------ | ------------------- |
| 2ኛ. | ------------------------------- | ------------------ | -------------------- |
| 3ኛ. | ------------------------------- | ------------------ | -------------------- |